# በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር

## የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት አፈፃፀም የውስጥ መመሪያ ቁጥር 491/2013

በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር
Records Section
የሬከርድና ማህደር ክፍል

ግንቦት 2012 ዓ.ም

# መመሪያ ቁጥር 491/2013
## በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር
## የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት አፈፃፀም የውስጥ መመሪያ

ሚኒስቴሩ በገንዘብ ሚኒስቴር የወጣውን የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት መመሪያ ቁጥር 51/2010 በተገቢው መንገድ ለማስፈፀም የስራ ክፍሎችን ተግባርና ኃላፊነት በመዘርዘር ተከታትሎ ማስተግበሩ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ይህንን መመሪያ አውጥቷል::

### ክፍል አንድ
### ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት አፈፃፀም የውስጥ መመሪያ ቁጥር **491/2013** ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ ያሉ ቃላትና ሃረጎች በፌደራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 (እንደተሻሻለው) በፌደራል መንግስት ግዥ እና የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 በሚኒስትሮች ምክር ቤት የፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 190/2002 እና በፌደራል መንግስት የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነትን መመሪያ ቁጥር 51/2010 የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ:: ከዚህ በተጨማሪ በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1) **"የስራ ክፍሎች"** ማለት ለህዝብ ይፋ የሚደረጉ የፋይናንስ ግልጽነትንና ተጠያቂነትን መረጃን በማዘጋጀትና በማሰራጨት ሂደት የሚሳተፉ የዕቅድ ዝግጅት ክትትልና ግምገማ ዳይሬክቶሬት የፋይናንስ ግዥ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት የውስጥ ኦዲት ዳይሬክቶሬት' የኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት የተለያዩ ፕሮጀክት ማስተባበሪያዎች እና ሌሎች እንደአስፈላጊነቱ የሚጨመሩ የሥራ ክፍሎች ናቸው::

2) **"ሚኒስቴር"** ማለት የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ነው።

3) **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው።

የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር
Records Section
የሪከርድና ማህደር ክፍል

3. **የተፈፃሚነት ወሰን**

ይህ መመሪያ በፌደራል መንግስት የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነትን መመሪያ ቁጥር 51/2010 መሰረት በሚኒስቴሩ ለህዝብ ይፋ እንዲደረጉ በሚዘጋጁና በሚያሰራጩ መረጃዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል::

4. **ዓላማ**

የዚህ መመሪያ ዓላማ የሚኒስቴሩ የስራ ክፍሎች:-

1) የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት መረጃዎችን በተዘረጋው የአሰራር ስርዓት መሠረት ዜጎች በቀላሉ ሊረዱት በሚችሉበት ዘዴ በወቅቱና በተሟላ መልኩ ተደራሽ እንዲያደርጉ በማድረግ ግልጽነት እና ተጠያቂነትን ማረጋገጥ፤

2) የዜጎች ተሳትፎን በማጎልበት የመንግስት ሀብት ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ ለታለመለት ዓላማ መዋሉን እና የህዝብ ተጠቃሚነትን በማረጋገጥ መልካም አስተዳደርን ማስፈን ነው::

5. **መርሆዎች**

የሚኒስቴሩ የስራ ክፍሎች ማንኛውንም የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት ተግባር ሲያከናውኑ የሚከተሉትን መርሆዎች መሠረት ማድረግ አለባቸው፡-

1) የመንግስት ፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት መረጃዎች ህብረተሰቡ ሊረዳው በሚችል መልኩ ተሟልቶ እና ወቅቱን ጠብቆ ተደራሽ መደረጋቸውን፣

2) የዜጎችን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የፕሮግራሙ ወይም የፕሮጀክቱ ወይም የተግባሩ ቀጥታ ተጠቃሚ የሆነው የህብረተሰብ ክፍል በበጀት ሂደቱ በተሟላ መልኩ የሚሳተፉበት ምቹ ሁኔታ የተፈጠረለት መሆኑና

3) በማንኛውም የበጀት ምንጭ የሚከናወኑ ፕሮግራሞች ወይም ፕሮጀክቶች ወይም ተግባራት በዕቅዱ መሰረት በቁጠባ በብቃት በጥራት እና በውጤታማነት የተከናወኑ እንዲሁም በአፈጻፀም የሚታዩ አሉታዊ ልዩነቶች ተጠያቂነት የሚያስከትሉ መሆኑን፤

የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር
Records Section
የሪከርድና ማህደር ክፍል

# ክፍል ሁለት
# ተግባርና ኃላፊነት

ለህዝብ ይፋ የሚደረጉ የየፋይናንስ ግልጽነትንና ተጠያቂነትን መረጃን በማዘጋጀትና በማሰራጨት ሂደት የሚሳተፉ የሚኒስቴሩ ስራ ክፍሎች የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት አለባቸው::

## 6. <u>የፋይናንስ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ተግባርና ኃላፊነት</u>

6.1) ሚኒስቴሩ የየሩብ ዓመት የሂሳብ ሪፖርት በመንግስት ሂሳብ ማንዋል ላይ በተገለጹት ቅጾች መሠረት በማዘጋጀት በየሩብ ዓመቱ መጨረሻ የዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 ባስቀመጠው የጊዜ ገደብ ለኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ያቀርባል፣

6.2) የሚኒስቴሩን የግዥ አፈጻጸም ሂደት በፌደራል መንግስት የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት መመሪያ አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት በአባሪ 5.2 ላይ በመሙላት የዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 ባስቀመጠው የጊዜ ገደብ አግባብ ለኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ያቀርባል፡፡

## 7. <u>የዕቅድ ዝግጅት፣ ክትትልና ግምገማ ዳይሬክቶሬት ተግባርና ኃላፊነት</u>

7.1) ለሚኒስቴሩ መ/ቤቱ የተመደበ በጀት በበጀት ዓመቱ ውስጥ ከልዩ ልዩ ምንጮች በጥሬ ገንዘብ የተገኘ እና በዓይነት የተገኘ የዕርዳታና የብድር ሂሳብ መረጃን በማካተት በፌደራል መንግስት የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት መመሪያ ቁጥር 51/2010 ጋር ተያይዞ በተላከው አባሪ 1.4 ላይ በመሙላት የዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 ባስቀመጠው የጊዜ ገደብ አግባብ ለኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ያቀርባል፣

7.2) የሚኒስቴሩን የተለያዩ ፕሮጀክቶች ዝርዝር መግለጫ መረጃዎችን በፌደራል መንግስት የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት መመሪያ ቁጥር 51/2010 ጋር ተያይዞ በተላከው አባሪ 4.1 እና 4.2 ላይ በመሙላት የዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 ባስቀመጠው የጊዜ ገደብ አግባብ ለኮሚዩኒኬኝን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ያቀርባል፣

7.3) የሚኒስቴሩ የፕሮግራሞች ውጤቶችና ግቦች ዓመታዊ የዕቅድና የየሩብ ዓመቱን የአፈጻጸም መረጃዎች በፌደራል መንግስት የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት መመሪያ ቁጥር 51/2010 ጋር ተያይዞ በተላከው አባሪ 4.3 ላይ በመሙት የዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 ባስቀመጠው የጊዜ ገደብ ለኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ያቀርባል፡፡

የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር
Records Section
የሪከርድና ማህደር ክፍል

## 8. የውስጥ ኦዲት ዳይሬክቶሬት ተግባርና ኃላፊነት

8.1) የሚኒስቴሩ የውስጥ ኦዲት ግኝት የተጠቃለለ ዓመታዊ የጥሬ ገንዘብ' ገቢ'ተሰብሳቢ'ግዠ' ንብረት ወጪ በጀት እና ኦዲት ክትትል ሂሳብ መረጃዎችን በፌደራል መንግስት የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት መመሪያ ቁጥር 51/2010 ጋር ተያይዞ በተላከው አባሪ 3 ላይ በመሙላት የዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 ባስቀመጠው የጊዜ ገደብ አግባብ ለኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ያቀርባል'

8.2) የሚኒስቴሩ የየሩብ ዓመት የ6 ወርና ዓመታዊ የበጀት ገቢና ወጪ ሂሳብ መረጃዎችን በዋና ዋና የሂሳብ መደቦች በመለየት የዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 ባስቀመጠው የጊዜ ገደብ አግባብ ለኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ያቀርባል፡፡

## 9. የኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ተግባርና ኃላፊነት

9.1) በፌደራል መንግስት የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት መመሪያ ቁጥር 51/2010 ክፍል ሁለት አንቀጽ 7 ስር የተዘረዘሩትን የመሥሪያ ቤቱ የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት ስራ ትግበራን በበላይነት ይመራል፤ ለአፈጻጸሙም የሚኒስቴሩን የስራ ክፍሎችን ያስተባብራል::

9.2) የሚኒስቴሩን የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት ስራን ከዕቅድ እስከ አፈጻጸም በበላይነት ያስተገብራል የአፈጻጸም አጠቃላይ ሪፖርት ለሚኒስቴሩ የበላይ ኃላፊ የዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 ባስቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት ያቀርባል::

9.3) የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት የስልጠናና ግንዛቤ መስጨበጫ መድረኮችን ያዘጋጃል ያስተባብራል

9.4) በፌደራል መንግስት የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት መመሪያ አንቀጽ 10 እና 13 የተዘረዘሩትን መረጃዎች ከመመሪያው ጋር በተያያዙት አባሪዎች አመላካቾች መሰረት ተዘጋጅተው እንዲቀርቡ ያደርጋል፡፡

የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር
Records Section
ሪከርድና ማህደር ክፍል

9.5) የሚኒስቴሩ መሠረታዊ የበጀት መረጃዎችን እና ሌሎች የመንግሥት የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት መረጃዎችን ከሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች በማሰባሰብ በፌደራል መንግስት የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት መመሪያ አንቀጽ 14 መሰረት የዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 ባስቀመጠው የጊዜ ገደብ አግባብ ይፋ ይደርጋል፡፡

9.6) የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት የአፈጻጸም መረጃዎችን እና ተሞክሮዎችን በድምጽና በምስል በመቅረጽ እና በጽሁፍ በማዘጋጀት ለዜጎች ተደራሽ ያደርጋል፡፡

## ክፍል ሦስት

10. <u>ለዜጎች እና ለባለድርሻ አካላት የሚገለጹ መረጃዎች</u>

ሚኒስቴሩ በፌደራል መንግስት የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት መመሪያ ቁጥር 51/2010 አንቀጽ 13 ንኡስ አንቀጽ 1 እስከ 3 የተመለከቱትን መሰረታዊ የመንግስት የበጀት መረጃዎችን በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ በኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት አማካኝነት ለዜጎች እና ለባለድርሻ አካላት ይፋ ያደርጋል::

11.<u>የመረጃ ማስተላለፊያ ዘዴዎች</u>

የኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት በፌደራል መንግስት የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት መመሪያ አንቀጽ 14 ስር በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ለዜጎች እና ለባለድርሻ አካላት በሚኒስቴሩ ድረ-ገጽ በቴሌቪዥን' በማህበራዊ ሚዲያ እና በማስታወቂያ መለጠፊያ ሰሌዳዎች በመጠቀም መረጃዎቹን ለሁሉም ተገልጋይ ተደራሽ ያደርጋል::

12.<u>የመረጃ ማተላለፊያ ጊዜ ሰሌዳ</u>

የሚመለከታቸው የሚኒስቴሩ የስራ ክፍሎች በፌደራል መንግስት የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት መመሪያ ቁጥር 51/2010 ክፍል ሦስት አንቀጽ 15 ስር ከተጠቀሰው የመረጃ ማስተላለፊያ ጊዜ ሰሌዳ ከ5 የስራ ቀናቶች በፊት በአባሪዎቹ መሰረት እንደ የስራ ክፍሉ ኃላፊነትና የስራ ድርሻ የተዘጋጁትን መረጃዎችን ለኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ያቀርባል::

የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር
Records Section
የመዝገብና ማህደር ክፍል

## ክፍል አራት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

13. ከተባባሪ አካላት ጋር የሚደረግ ጥምረት

13.1) የሚመለከታቸው የሚኒስቴሩ የስራ ክፍሎች የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት ስርዓትን ሲተገብሩ ከሌሎች የዜጎች ሁለንተናዊ ተሳትፎ ተግባሪ አካላት (የማህበራዊ ተጠያቂነት) ቅሬታ ሰሚ አካላት እና ከሌሎች ጋር በጥምረት መስራት መረጃ መለዋወጥና የዜጎችን ተሳትፎ ሊያሳድግ በሚያስችል ተግባራት ላይ አብሮ መስራት ይኖርባቸዋል::

13.2) ሚኒስቴሩ በመደበኛ በብድርና እርዳታ የበጀት ምንጭ የሚከናወኑ የካፒታል ፕሮጀክቶች ዕቅድና የበጀት አፈጻጸም ላይ በሠራተኞቹ እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ሩብ ዓመቱ በተጠናቀቀ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ መወያየት ይኖርበታል::

13.3) ሚኒስቴሩ የተለያዩ ፕሮጀክቶች በሚከናወኑበት ቦታዎች ሁሉ ከአካባቢው ህብረተሰብና ከባለድርሻ አካላት ጋር ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ በአፈጻጸሙ ላይ ምክክር መደረግ አለበት::

13.4) ከላይ በአንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 13.2 እና 13.3 መሰረት በሚደረገው ውይይት ላይም የሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች ከተሰጣቸው ተግባርና ኃላፊነት አንፃር ተገቢውን መግለጫ ማቅረብ ይኖርባቸዋል::

13.5) የተለያዩ ፕሮጀክቶች አፈጻጸምና ሂደት ላይ እንዲሁም በጥናቶች ሪፖርት ላይ ሚኒስቴሩ የሚመለከታቸውን በመጋበዝ መወያየት ይኖርበታል::

14. አስተዳደር እርምጃዎች

በዚህ መመሪያ የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት ኃላፊነት በተመለከተ የተሰጠውን ኃላፊነት በአግባቡ በማይወጡ የስራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ላይ በመመሪያ ቁጥር 48/2009 ላይ በተደነገገው አስተዳደራዊ እርምጃ እንደአስፈላጊነቱ ተፈፃሚ ይሆናል::

የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር
Records Section
የመዝገብና ማህደር ክፍል

15. **<u>ተፈፃሚነት የማይኖራቸው መመሪያዎችና ልማዳዊ አሠራሮች</u>**

ይህን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሠራር በዚህ መመሪያ ውስጥ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

16. **<u>መመሪያውን ስለማሻሻል</u>**

ሚኒስቴሩ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ይህን መመሪያ ሊያሻሽለው ይችላል።

17. **<u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ መመሪያ ከግንቦት 14 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል።

ሂሩት ካሳው ወንድም (ዶ/ር)
የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር
ሚኒስትር

የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር
Records Section
የሪከርድና ማህደር ክፍል